አፍሪካ፤ ከመለያየት አባዜ ህብረት ወደማጠናከር!

ብ. ነጋሽ

የአፍሪካ ህብረት 28ኛ መደበኛ ስብሰባውን ጥር 22 እና 23፣ 2009 ዓ/ም በአዲስ አበባ አካሂዷል። ህብረቱ በዓመት ሁለቴ ነው መደበኛ የመሪዎች ጉባኤ የሚያካሂደው፤ አንደኛው፤ ሁሌም የህብረቱ ዋና ጽህፈት ቤት በሚገኝበት አዲስ አበባ፤ ሌላኛው የዓመቱ የህብረቱ ሊቀመንበር በሚመራው አገር ይካሄዳል። የዘንድሮው 2ኛ ጉባኤ የህብረቱ ሊቀመንበር ሆነው የተመረጡት አልፋ ኮንዴ በፕሬዝዳንትነት በሚመሯት ጊኒ ይካሄዳል። እናም የአፍሪካ ህበረት ጉባኤ በአዲስ አበባ መካሄዱ በራሱ እንግዳ ነገር አይደለም። ላለፉት ሃምሳ ዓመታት በቋሚነት ሲካሄድ የኖረና የተለመደ ነው።

ምናልባት የዘንድሮውን የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ ልዩ የሚያደርገው ከወራት በፊት በኤርትራ መንግስት ማስታወቂያ ሚኒስቴር አቅጣጫ እየተሰጣቸው የሚሰሩ የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች የነዙት ወሬ ነው። ይህም በኢትዮጵያ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ እንዲታወጅ ያስገደደ የጸጥታ ችግር ስላለ 28ኛውን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች መደበኛ ስበሰባ ችግር ይገጥመዋል በሚል የተነዛ ነው። እነዚህ የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች ይህን ወሬ ያገኘነው ከህብረቱ ኮሚሽን ሊቀመንበር ዶ/ር ኒኮሳዛና ድላሚኒ ዙማ ነው ነበር ያሉት፤ ሆኖም የኮሚሽኑ ሊቀመንበር ይህን ማለታቸውን የሚያረጋግጥ አንዳችም ማስረጃ አልተገኘም። በመሆኑም ወሬው የፈጠራ ነበር። ወሬው በተነዛበት ወቅት የኢትዮጵያ መንግስት ጉዳዩን እንደቁም ነገር ቆጥሮ ምላሽ አለመስጠቱም ተራ የፈጠራ ወሬ እንደነበረ ያመለክታል።

ያም ሆነ ይህ፤ 28ኛው የአፍሪካ ህብረት መደበኛ የመሪዎች ስብሰባ ፍጹም ሰላማዊና ስኬታማ ሆኖ ተጠናቅቋል። ጉባኤው አርባ ገደማ የአፍሪካ አገራት መሪዎች፣ የሌሎች አህጉራትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች መሪዎች፣ በቪአይፒ ሳሎን ያለፉትን ሳይጨምር ከ3 መቶ በላይ የተለያዩ አገራት እና ሚዲያ ተቋማት ጋዜጠኞች፣ የአገር ውስጥ ጋዜጠኞችና ሌሎች እንግዶች፤ በድምሩ ከ4 ሺህ በላይ ሰዎች ተሳትፈውበታል። እርግጥ፤ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ጉባኤው በዚህ አኳኋን እንደሚካሄድ አስቀድሞም እምነት ነበራቸው። መደበኛ ጉባኤው እንዳይካሄድ የማድረግ ከንቱ ህልም የነበራቸው የኤርትራ መንግስትና የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ነን በሚል ሽፋን የሚንቀሳቀሱ የትርምስ ስትራቴጂ አስፈጻሚዎች ብቻ ናቸው።

የጉባኤውን ሰላማዊነት አስመልክቶ በተሳታፊዎች ከተሰጡ አስተያየቶች መካከል አንድ ሁለቱን ልጥቀስ። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ልዩ አማካሪ ማገድ አብድላዚዝ፣ በአገሪቱና በአዲስ አበባ ያለውን ሰላም አስመልክተው በሰጡት አስተያየት፣ ሃገሪቱ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሥር ያለች አትመስልም፤ ምንም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምልክት የለም። ስብሰባውም በሰላም ተጠናቅቋል። ሰላምን የሚያደፈርስ ምንም አይነት ችግር አላየሁም፤ ብለዋል። በአዲስ አበባ የተለያዩ አካባቢዎች መዘዋወራቸውንና ምንም አይነት የጸጥታ ችግር እንዳላጋጠማቸው፣ ሌሎች የጉባኤው ተሳታፊዎችም ወደፈለጉበት ቦታ ያለምንም ገደብና ቁጥጥር በመንቀሳቀስ አገልግሎት ሲያገኙ እንደነበረ መመልከታቸውንም ተናግረዋል። በተመሳሳይ በአፍሪካ ህብረት የኢንዱስትሪ ክፍል ኃላፊ ሃሰን ሁሴን በሰጡት አስተያየት፤ በኢትዮጵያ ሰላም አለ፤ በአገሪቱ ያለው ሁኔታም መልካም ነው፤ ብለዋል። ይህም አገሪቱ ሰላምና ልማትን በማረጋገጥ ረገድ በትክክለኛ ጎዳና ላይ መሆኗን አመላካች መሆኑንም ገልጸዋል።

በአገሪቱ ጠላቶችና በጉዳይ አስፈፃሚዎቻቸው የተሞከረው ጉባኤውን የማክሸፍ ህልም በዚህ አኳኋን ቅዠት ሆኖ መቅረቱ አንድ ጉባኤውን በልዩነት እንድናስታውስ የሚያደርገን ጉዳይ ነው።

ሌላው በእኔ እይታ 28ኛውን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ልዩ የሚያደርገው፤ በአውሮፓና በአሜሪካ ከሚታየው አዝማሚያ የተለየ እውነታ የተንጸባረቀበት መሆኑ ነው። በቅርቡ እንግሊዝ ከአውሮፓ ህብረት አባልነት ራስዋን አውጥታለች። በሌሎችም የአውሮፓ አገራት ተመሳሰይ ዝንባሌዎች እየተንጸባረቁ ነው። አዲሱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ እንግሊዝ ከአውሮፓ ህብረት መውጣቷን አወድሰውታል። ፕሬዚዳንት ትራምፕ ከአገራት ጋር ከመቀራረብ ይልቅ መፋታተን ነው የመረጡት፤ ትራምፕ ፕሬዚዳንት ሆነው በተመረጡ ማግስት አገራቸው ካናዳን፣ አውስትራሊያን፣ ጃፓንን፣ ሜክሶኮን ጨምሮ 12 አገራትን በአባልነት ካቀፈው Trans Pacific Partnership (TPP) አባልነት እንድትወጣ አድርገዋል። ከሰሜን አሜሪካ ነጻ የንግድ ስምምነት (North America Free Trade Agreement _ NATFA) የመውጣት ፍላጎት እንዳላቸውም በምርጫ ፉክክር ዘመቻቸው ሲገልጹ እንደነበረ ይታወሳል።

ታዲያ በዘንድሮው የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ ላይ በአውሮፓና በአሜሪካ ከሚታየው የመለያየት አዝማማያ በተቃራኒ ከህብረቱ አባልነት ራሷን አግልላ ለ33 ዓመታት ያህል የቆየችው ሞሮኮ ወደአባልነት ለመመለስ ጥያቄ አቅርባ ህብረቱ ጥያቄውን ተቀብሎ አጽድቋል። የአውሮፓ አገራትና አሜሪካ ወደመለያየት ሲሄዱ አፍሪካውያን ዘንድ ደግሞ ወደመተባባር የመሄድና ህብረትን የማጠናከር አዝማሚያ ታይቷል። ይህ የዘንድሮውን የአፍሪካ ህብረት መደበኛ ጉባኤ ልዩና ታሪካዊ ያደርገዋል።

28ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ባለፉት አራት ዓመታት የህብረቱን ኮሚሽን በሊቀመንበርነት በመሩትና የስራ ዘመናቸውን በጨረሱት ኒኮሳዛና ዴላሚኒ ዙማ ምትክ ቻዳዊውን ሙሳ ፋቂ መሃማት የህብረቱን ኮሚሽን ለቀጣይ አራት አመታት በሊቀመንበርነት እንዲመሩ መርጧል። ጋናዊው ክዌሲ ቋርቴይ ደግሞ ምክትል ሊቀመንበር ሆነው ተሰይመዋል። የህብረቱ ኮሚሽን ሊቀመንበር ሆነው

የተመረጡት የ56 አመቱ ሙሳ መሃማት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ2003 እስከ 2005 ዓ.ም የቻድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው አገልግለዋል። ከ2007 እስከ 2008 ባለው ጊዜም የአገሪቱ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሆነው ሰርተዋል። በተመሳሳይ ወቅት የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነውም አገልግለዋል።

28ኛው የአፍሪካ ህብረት መደበኛ ጉባኤ በርካታ አህጉራዊ ውሳኔዎች የተላለፉበትም ነበር። ህብረቱ ካሳለፋቸው ውሳኔዎች ዋና ዋናዎቹ መካከል፤ በአህጉሪቱ የገበያ ትስስርን ለመፍጠርና በ2020 ከግጭት የፀዳች አፍሪካን ማየት የሚለው ቀዳሚው ነው። በሊቢያ፤ በሶማሊያ እና በደቡብ ሱዳን የሚታየውን የሰላምና የፀጥታ ችግር ለመፍታት የሚያስችል አቅጣጫም አስቀምጧል። በአፍሪካ አንድ የጋራ ገበያ ለመፍጠር አባል አገራቱ መግባባት ላይ ደርሰዋል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የ2030 የዘላቂ ልማት ግቦችና የአፍሪካ የ2063 የሰላምና የብልፅግና ግብ ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ማድረግ በሚያስችል አጀንዳ ላይም ስምምነት ተደርሷል። ህብረቱን በፋይናንስ ለመደገፍም አባል ካልሆኑ አገራት ወደአባል አገራት በሚገቡ ምርቶች ላይ የዜሮ ነጥብ 2 በመቶ ቀረጥ የመጣል ስምምነትም ላይ ተደርሷል። በእነዚህ ውስጥ የሴቶችንና የወጣቶችን ተጠቃሚነትና ከዚህም ጋር ተያይዞ አጠቃላይ የአህጉሪቱን ህዝቦች ኑሮ ማሻሻል የሚያስችሉ ጉዳዮች ተነስተው ውሳኔ ተላልፎባቸዋል።

ከዚህ በተጨማሪ፤ የአፍሪካ የሰላምና የፀጥታ ምክር ቤት የ2016 ሪፖርት ቀርቦ የመፍትሄ አቅጣጫዎችንም አስቀምጧል። በዚህም በ2016 የሰላምና ፀጥታ ችግር አለባቸው ያላቸውን አገራትና የሚወሰዱ የመፍትሄ ሃሳቦችንም ይፋ አድርጓል። ምክር ቤቱ ጋምቢያ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሶማሊያ፣ ማሊ፣ ሊቢያ፣ ብሩንዲ፣ ጊኒ ቢሳው እና ምዕራባዊ ሰሃራ የሰላምና ፀጥታ ችግር ያለባቸው በሚል ለይቷል። በጋምቢያ ተካሂዶ በነበረው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ የአዳማ ባሮውን ማሸነፍ ተከትሎ ተፈጥሮ የነበረው ችግር፣ በምዕራብ አፍሪካ አገራት የኢኮኖሚ ማህበረሰብ (ኢኮዋስ) እና በህብረቱ ጥረት መፈታቱንም አንስቷል።

የአፍሪካ የሰላምና የጸጥታ ምክር ቤት የደቡብ ሱዳን ተቀናቃኝ ሃይሎችም በ2015 የገቡትን ቃል እንዲተገብሩ ጥሪውን አቅርቧል። በደቡብ ሱዳን ወደ ብሄር ያመራውን ግጭት ለመፍታትም ሁሉንም ወገኖች ያሳተፈ ውይይት እንዲካሄድ አቅጣጫ አመላክቷል። መንግስትም የአፍሪካ ቀጣና የሰላም ጥበቃ ሃይል ወደ ስፍራው እንዲገባ እንዲፈቅድና ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጋር በጋራ እንዲሰራ ጠይቋል። አገራትና መንግስታት ችግሩን ለመፍታት የገንዘብ ድጋፍ ያደርጉ ዘንድም ጥሪውን አቅርቧል።

በሶማሊያ በህብረቱ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ (አሚሶም) ወታደሮች ክፍያ መቀነስ ጋር ተያይዞ ለተከሰተው ችግር አባል ሃገራቱ ድጋፍ እንዲያደርጉ የህብረቱ የጸጥታ ምክር ቤት ጠይቋል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤትም ለህብረቱ ድጋፍ እንዲያደርግ ጠይቋል። በመጨረሻም በ2020 ዓ.ም ከግጭት የጸዳች አፍሪካን ለመገንባት አገራት ጠንክረው ሊሰሩ ይገባል ሲል አሳስቧል። ለዚህም የግጭት መንስኤ የሆኑትን የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና ጅኦ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን መፍታትና የባህር ላይ ዝርፊያንና ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን መግታት እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥቷል።

የአፍሪካ ህብረትና የህብረቱ የሰላምና ጸጥታ ምክር ቤት ያሳለፏቸው ውሳኔዎች በሙሉ ኢትዮጵያ ከምትከተለው የልማትና የሰላም ስትራቴጂ ጋር ያጣጥማል። ህብረቱ የ2063 የሰላምና የብልጽግና ግቡ አካል እንዲሆን የወሰነው የተባበሩት መንግስታት ዘላቂ የልማት እቅድ የኢትዮጵያ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አካል ሆኖ በመተግበር ላይ ይገኛል። ኢትዮጵያ አህጉሪቱን በንግድ የማስተሳሰሩን እቅድ በተለይ እስከ ሰሜን አፍሪካ በሚዘልቅ የቀጣናው የሃይል ትስስር እቅድ ነድፋ ተግባራዊ ማድረግ ጀምራለች። ላለፉት ሃያ ዓመታትም ለአህጉሪቱ በተለይ ለምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ሰላምና መረጋጋት ልዩ ትኩረት ሰጥታ በግንባር ቀደምትነት እየተንቀሳቀሰች መሆኗም ይታወቃል። ይህ ኢትዮጵያ ህብረቱን እንድትደገፍ ህብረቱም የኢትዮጵያን እቅድ አፈጻጸም እንዲደግፍ የሚያደርግ ሁኔታን በመፍጠር ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል።

በአጠቃላይ ሰሞኑን በኢትዮጵያ በአዲስ አበባ የተካሄደው የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ አፍሪካውያን ከመቼውም ጊዜ በተሻለ ግልጽነት ለሰላምና ለብልጽግናቸው በህብረት እንዲቆሙና ህብረታቸውን እንዲያጠናክሩ ማድረግ የሚያስችል ውሳኔ የተላለፈበት ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ፤ በአሜሪካና በአውሮፓ ከሚታየው መለያየትና አንዱ በሌላው ላይ በሩን ከመዝጋት የኋሊት አካሄድ በተለየ ህብረትን የማጠናከር አዝማሚያ የታየበት ነው። ይህም የአፍሪካን የህዳሴ ዘመን መጀመር ያበስራል።